# መጋደሙ አበሰበሰው እንጂ ማለፍያ አላሳጣንም

የጦርነት እንጂ የልማት አጀንዳ የሌለው የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያ በሕዝቧና በመንግስት ሁለንተናዊ ጥረት እያስመዘገበች ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ እንቅፋት ሆኖ መጋደም ዋንኛ ስራው ሆኗል። የኢትዮጰያ መንግሥት አቋም ደግሞ አንድና አንድ ነው።

ሻእብያ ኢትዮጰያ የጀመረችውን ፀረ ድህነት ትግል ለማደናቀፍ አንዴ በሰሜን ሌላ ጊዜ ደግሞ በምስራቅ ትልቅ ግንድ ሆኖ ሲጋደም ውሎ ያድራል እንጂ በቀኝም በግራም ብለን ማለፍ እስከቻልን ድረስ የሱ መጋደም ጉዳያችን አደለም የሚል።በተለያየ አቅጣጫ የሚጋደም ግንድ የመበስበሻ ጊዜውን በተወሰነ ደረጃ ከማራዘሙ በቀር መበስበሱ አይቀሬ ነው። የኢትዮጰያ መንግሥት ደግሞ በቀላል ወጪ ነገር ግን አድካሚ ማለፍያ አፈላልጎ ግንዱን ለመሻገር እድል እስካገኘ ድረስ የጀመረውን ፈጣን የልማት እድገት ማስቀጠል ምርጫው አድርጎታል።

ኢትዮጰያ ካስመዘገበችው እድገት እኔ ምን ያህል ተጠቅምያለሁ በሚለው ላይ ልዩነት ይኖር እንደሆን እንጂ የፈጣን የልማት ጎዳና መያዝዋ በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ስምምነት ላይ የተደረሰበት የአደባባይ ሚስጢር ሆኗል። በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት በሁሉም ዘርፍ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል።ሃገሪቱ ለስድስተኛ ጊዜም ተመሳሳይ እድገት በአስተማማኝ ሁኔታ ለመድገም በሚያስችላት አቋም ላይ መሆንዋን ስምዋን በደግ ሲያነሳ ያልነበረው ዘ ኢኮኖሚስት ሳይቀር እ.አ.አ. በ2009 ፈጣን እድገት ከሚያስመዘግቡ አስር አገሮች ውስጥ በአራተኛ ደረጃ አስቀምጧታል።

በአንፃሩ ሻእብያ አሁንም በውኑ በህልሙ የቀድሞዎቹ ፊውዳላዊ አስተሳሰብ በተግባርም በአዋጅም መግለፁን ቀጥሎበታል። ኢትዮጰያ ሲባል ብሄር ብሄረሰቦችዋ እነሱን አንድ አድርጎ ያቆመው ህገ መንግሥት አያስቀኑትም። ይልቁንም የልዩነትና የጥፋት ምንጭ አድርጎ ይወስዳቸዋል። ለሻእብያ ከዚህ ባሻገር በኢትዮጰያ "ተፈጥሮ ፀጋዎች" ላይ መቋመጥ ይዘዋል የሶሞኑ የሃገሪቱ ፕሬዝዳንት መግለጫ እንዳመለከተው። የሰሜኑ ሰሊጥ የደቡቡ ቡና የምስራቁ ሰንጋ ወዘተ በአይናቸው ውል እንዳለ በተጋደመበት ቀንና ሌት ይፈራረቃል።

የኤርትራ መንግሥት ይህ ስስቱ አንደፋድፎ የዛሬ ዘጠኝና አስር አመት ወደ ጦርነት ካስገባው ሽንፈት መማር አቅቶት በምስራቅ በኩል መጣሁባቹህ እስካለን ድረስ ያደረጋቸው እኩይ ድርጊቶች ላይ መንግሥት የነበረው አቋምና የተለያዩ ወገኖች መወሰድ ነበረበት ያሏቸውን እርምጃዎች መካከል ያለው ልዩነት ለመመልከት የሚያስችለን ዳሰሳ እናድርግ።

አንዳንዶቹ የኤርትራ መንግሥት የአክራሪዎች ማሰልጠኛ ተቋማት ከፍቶ የሚያሰለጥንባቸው ኤርትራ ውስጥ ነበሩ ይላሉ። የኤርትራ መንግሥት የጦር መሪዎች ሶማልያ ውስጥ ገብተው ከአክራሪዎች ጋር የጦር አመራርም ይሰጡ እንደነበርም በወቅቱ ተገልጿል። ወደ ኢትዮጵያ ሰርጎ በመግባት የሚያሸብርና የልማት እንቅስቃሴን የሚስተጓጉል ሃይልም እስከ መመስረት እንደደረሰ የትላንት ትውስታችን ነው።

እነዚህን ለማስታወስ ቢያንስ አንዳንድ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በወቅቱ ያሰራጩትን ዘገባ እንመልከት።

**<u>ኤን ቢ ሲ ኒውስ የተሰኘው የአሜሪካ ቴሌቪዥን ጣቢያ</u>**

የሻእቢያ መንግስት በሶማሊያ ተሰባስቦ ለነበረው የአክራሪ ቡድን ቀጥተኛ አመራርና የተለያዩ ድጋፎችን ከመስጠት በተጨማሪ በህገ ወጥ መንገድ ከፍተኛውን የጦር መሳሪያ ሲያቀርብ እንደነበርና በተመሳሳይ መንገድ ከሌሎች አገሮች ለአሸባሪው ቡድን ሲሰጡ የነበረውን የጦር መሳሪያ የኤርትራ መንግሥት ተቀብሎ ወደ ሶማሊያ ሲያስገባ ቆይቷል።

ኤን ቢ ሲ ኒውስ በሶማሊያ ላይ የጦር መሳሪያ ማእቀብ ተጥሎ በነበረበት ወቅት ማእቀቡን እንዲከታተል በመንግስታቱ ድርጅት የተሰየመው ቡድን በህዳር 1999 ባወጣው ሪፖርት ይፋ አድርጎታል። በሪፖርቱ የሻእቢያ መንግሥት  የጦር መሳሪያ ከማቅረብ ባሻገር  ተደምስሶ ከተበታተነው ከአክራሪው የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት አመራር፣ የጦር መኮንኖችና የፖለቲካ መሪዎች ጋር ውይይት በማድረግ አመራር ሲሰጥ ቆይቷል።

ሻእቢያን ጨምሮ አንዳንድ ፀረ-ኢትዮጵያና የአሸባሪው ቡድን ደጋፊ የሆኑ አገሮች መንግሥታት የጦር መኮንኖች  በደረሰበት ሽንፈት ከተበታተነው የአክራሪው ቡድን የፋይናንስ ኃላፊ ጋር በነሐሴ 1999  ሶማሊያ ውስጥ ተሰብስበው ነበር። በዚሁ ስብሰባ በሶማሊያ የአሸባሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም መክፈት በሚቻልበት መንገድ መምከራቸውንና በመስከረም ወር ደግሞ የመጀመሪያዎቹን አሸባሪዎች ማሰልጠን መቻላቸውን ዘገባው አትቷል።

በዚያው ዓመት ነሐሴ 20 ቀን ንብረትነቱ የዳሎ አየር መንገድ የሆነ ኤ 310_300 ኤርባስ አውሮፕላን ከኤርትራዋ የወደብ ከተማ አሰብ ተነስቶ ወደ ሶማሊያ መግባቱንም ሪፖርቱ በማስረጃ ማረጋገጡንም ኤን ቢ ሲ ኒውስ ዘግቦ ነበር። ይኸው ከኤርትራ የተነሳው አውሮፕላን ፀረ ታንክ፣ ማሽን ጋን፣ ሞርታርና ፒኬኤም የተሰኘ ከባድ መሳሪያን ጨምሮ በርካታ ወታደራዊ ቁሳቁሶችን ጭኖ እንደነበርም ተጠቅሷል። ከምድር ወደ አየር የሚወነጨፍ ሚሳይል ጨምሮ ለተንቀሳቃሽ የውጊያ መሳሪያዎች የሚያገለግሉ ከባድ ኦቶሞቢሎች፣ ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪዎችና  የሞተር ብስክሌቶች ማራገፉንም የመንግሥታቱ ድርጅት ሪፖርት ይፋ አደረገ። ከዚህም በተጨማሪ ሻእብያ በምስራቅ በኩል ኢትዮጳያን ለመበታተን ሲጥር ዝም ብሎ መታየት የለበትም የሚሉ ወገኖች ድምፅ በዚህ ወቅት ጎልቶ ተሰማ።

ይባስ ብሎ ከተለያዩ የውጭ አሸባሪ ኃይሎች በሚሊዮኖች ዶላር  የሚቆጠር ገንዘብ ሲጎርፍለት የነበረው የሶማሊያ አክራሪ ቡድን እንዴት ጥቅም ላይ ይዋል የሚለው የእቅድ አውጪ ሊቅ ሻእቢያ እንደነበረ ሪፖርቱ ጉዳዩን አጠናከረው። በተለያዩ የአሸባሪው ቡድን ደጋፊ አገሮች መንግሥታት አማካኝነት የሌሎች አገሮች ተዋጊዎችን ለምልመላ፣ ፈቃደኛ አሸባሪዎችን ለማሰባሰብ፣ በሶማሊያ የተለያዩ ወታደራዊ ካምፖችን ለማቋቋምና መደበኛ የወታደራዊ ስልጠናን ለመጀመር የሚያስችሉ ድጋፎች በስፋት ለማንቀሳቀስም ዕቅድ ተነድፎ ነበር።እቅዱን ተፈፃሚ ለማድረግም በሚስጢር ወደ ሶማሊያ ይላኩ የነበሩ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ህገ ወጥ  የጦር

መሳሪያዎችና ሌሎች ወታደራዊ ቁሳቁሶች በአየርና በባህር እየተጓጓዙ በየቀኑ ሞቃዲሾ በገፍ መግባት ጀምረው እንደነበም ነው የተዘገበው።

## በዘርፉ የአለም አቀፍ ተመራማሪዎች ቁጣ

ኒውዮርክ የሚገኘው የዓለም ፖሊሲ ምርምር ኢኒስቲትዩት ከፍተኛ ተመራማሪ ናቸው ዊሊያም ሃርተንግ። በሶማሊያ ላይ የጦር መሳሪያ ማእቀብ ተጥሎ በነበረበት ወቅት ማእቀቡን እንዲከታተል በመንግሥታቱ ድርጅት የተሰየመው ቡድን በህዳር 1999 ያወጣውን ሪፖርት አስመልክተው የሰጡት አስተያየት በመንግሥታቱ ድርጅት በጦር መሳርያ ዝውውር አለም ምን ያህል ልል አቋም እንዳለው ያሳየ ነበር ይላሉ። "ሪፖርቱ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ንግድ ሙሉ በሙሉ ከቁጥጥር ውጭ መውጣቱን የሚያሳይ ጥሩ ጥናት ነው" ብለዋል በወቅቱ።

እንዲህ አይነት የተቀነባበረ ግልፅና ወቅታዊ አደጋ ተጋርጦበትም ቢሆን መንግሥት ጉዳዩ በሰላም ከተፈታ እሰየው ብሎ ጥረቱን ቀጠለ። በተለያዩ ሀገሮች ለአብነት በሱዳን፣ በየመን፣ በዱባይ ራሱን እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ብሎ ከሚጠራው ሃይል ውስጥ ከነበረው አክራሪ ቡድን ጋር ሳይቀር ለመነጋገር ጥረት አደረገ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ችግሩን በመነጋገርና በድርድር በሰላም ለመፍታት የተደረገው ዲፕሎማሳዊ ጥረት በአክራሪው የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ሕብረት አሻፈረኝ ባይነት ሳይሳካ ቀረ።

ያም ሆኖ ግን መንግሥት የተቃጣብንን ግልጽ፣ ተጨባጭና ወቅታዊ አደጋ ለመቀልበስ የመጨረሻ መፍትሄ የሆነውን የኃይል አማራጭ በግብታዊነት አልወሰደም። ራስን የመከላከል መብትና ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ህግና ስርዓትን ተከትሏል።ጉዳዩን ለሀገራችን ካቢኔና ፓርላማ አቅርቦ ሰፊ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ጸድቋል።

ውሳኔውን መሰረት በማድረግም በክልሎች የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው ሕዝቡ በጉዳዩ ላይ በግልጽ ተወያይቶ የተጋረጠብን አደጋ በፍጥነት እንዲቀለበስ ከፍተኛ ድጋፍ እንዳለው አረጋገጠ።የሶማሊያ ሽግግር መንግሥትና ፓርላማ ይፋ ጥሪ ተቀብሎም ወደ ሶማሊያ ዘልቆ የመግባትና እዛው የመቆያ ጊዜውም አራዘመ።

መከላከያ ሠራዊታችንም በተሰጠው ግዳጅ በኤርትራ መንግሥት አቀነባባሪነትና መሪነት በሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ሕብረት ውስጥ በነበሩ አክራሪ ኃይሎችና በውስጥ አፍራሽ ኃይሎች ተባባሪነት ተደቅኖብን የነበረውን አደጋ በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ አመከነ።የኢትዮጵያን ድህንነት አስጠብቆ በክብርና ሞገሱን ግልጽ ባደረገው ቀነ ገደብ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። አመላለሱም ይፋ ኮቃድሾ ጀምሮ እስከ ኢትዮ ሶማሊያ ድንበር ድረስ በይፋ አቀባበልና አሸኛኘት ላይ የተመሰረቱ ነበሩ። አሸባሪዎቹ እግር በእግር ተከትለን ሶማሊያ መሬት ውስጥ እናስቀረዋለን ያሉት መከላከያ ሰራዊታችን ያለ አንዳች እንቅፋት በሶማሊያ ሰላም ወዳድ ሃይሎች በክብር ተሸኘ።ይህም አክራሪዎቹ ከተራ አሸባሪነት እንዳያልፉ ለማድረግ የተወሰደው ቀዳሚ የኢትዮጲያ ሰራዊት ተልእኮ መሳካቱን ዳግም መሰከረ።

ይህ ብቻ አልነበረም የሠራዊታችን ስኬት ሚስጥር። አሸባሪውን ኃይል በመታበት ወቅትም ቢሆን አንድም ንጹህ ሰው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የከፈለው ታላቅ መስዕዋትነትና ያደረገው ጥንቃቄ የሶማሊያ ሕዝብ በመከላከያ ሠራዊታችን ላይ አመኔታ እንዲያሳድር አድርጎታል። በዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም መስፈን በጽናት የሚታገል፣ችግሮችን በመቻቻል፣ በውይይትና በድርድር የመፍታት እንዲሁም በሰላም ጠቀሜታ በጽኑ የሚያምን፣ ኃላፊነት የሚሰማው መሆኑንና ሰላም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጽኑ ፍላጎት መሆኑን አመላክቷል።

በርግጥ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በሶማሊያ ተልዕኮውን ለማሳካት ተገቢውን ሚና አልተጫወተም።ሃያላን አገሮች የሶማሊያ ጉዳይ ብሄራዊ ጥቅማቸውን የሚነካ አድርገው አልወሰዱትም። ይልቁንም ሶማሊያን ወላጅ አልባ አድርገው ትተዋታል። የሽግግር መንግሥቱ በተደራጀ መልኩ ባለመቀጠሉ ምክንያት የተፈለገውን ያህል መጓዝ እንዳልተቻለም መገመት ይቻል ይሆናል። እነዚህ አካላት ያልተሸከሙት ተሸክሞ መከላከያ ሰራዊታችን ጥላቻ ሰፍኖባት በነበረ ሶማሊያ ጎሳዎችና ታጣቂ ነጋዴዎች በማስታረቅ ጭምር ላለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ሰላምና መረጋጋት እርቋት በቆየችው ሶማሊያ አንጻራዊ የሰላም እንዲሰፍን አጋጣሚ ፈጥሯል።

በሶማሊያ አንጻራዊ ሰላም ሰፍኖ የሶማሊያና የኢትዮጵያ ወዳጅነት የሚጠናከርበት ብሩህ ተስፋ እናስብ። ምክንያቱም የአፍሪካ ሕብረት ሰላም አስከባሪ ኃይል ለማጠናከር ጥረት የሚደረግበት የተባበሩት መንግስታት ክፍተት እንዳይፈጠር መንግሥታት ሠራዊታቸውን በሶማሊያ ባሰማሩበትና ሌሎች ሀገሮችም ሠራዊታቸውን ለማስማራት የገቡት ቃል ለመተግበር እንቅስቃሴ ጀምረዋል። የሶማሊያ የሽግግር መንግስትና ተቀናቃኝ ወገኖችም በርካታ መቀመጫ ያለው የሽግግር መንግስት ፓርላማ ለመመስረት ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

በሶማሊያ ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ለማስፈንም ኢትዮጵያ ኃላፊነት የተሞላበት ጥረትዋ ትቀጥላለች። የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ሥዩም መስፍን በቅርቡ እንደገለጹት የኢትዮጵያ መንግሥት ለሶማሊያ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ድጋፍ በሙሉ አድርጓል። ወደፊትም እንደማንኛውም ጎረቤት ሀገር ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል። "ሠራዊታችን ከሶማሊያ ወጣ ማለት እጃችንን አጣጥፈን እንቀመጣለን ማለት አይደለም። ምክንያቱም ሶማሊያ ወደ ሥርዓትና ወደ ተሻለ ሰላም ካልተሸጋገረች ሁል ጊዜ አካባቢያችን እየታመሰ እንደሚቀጥል ማወቁ ለሁላችንም ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ ።" ነበር ያሉት።

በአንፃሩ የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያ የጀመረችውን የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዞ ለማደናቀፍ ጠንስሶት የነበረው ሴራ መና ቀረ። በተለይ በአሁኑ ወቅት በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ በመግባቱ የሀገሩን ዜጎች የትኩረት አቅጣጫ ያስቀየረ መስሎት ሠራዊታችን በሶማሊያ የነበረው ቆይታ ስኬታማ እንዳልነበረ አድርጎ የተለመደውንና ዓለም የሰለቸውን የበሬ ወለደ መሰረተ ቢስ ፕሮፓጋንዳውን ከመንዛት አልተቆጠበም። እውነታው ግን የሠራዊታችን ወደ ሶማሊያ መግባት ሁኔታውን ሊያባብሰው ይችላል በሚል ስጋት እንዳይገባ ሲከራከሩ የነበሩትን የአሜሪካ ማዕከላዊ ኮማንድና የዓለም ተንታኞችን ጭምር ሳይቀር ባስገረመና ባስደነቀ መልኩ ሠራዊታችን ተልዕኮውን በሁለት ሳምንታት ውስጥ በተሳካ መንገድ አጠናቋል።

ኢትዮጲያ ወደ ሙሉ ጦርነት መግባት ማለት ውስጡ ባዶ ከሆነ ግንድ ጋር መጋጨትም ቢሆን አደጋውን ጠንቅቃ በማወቅ በምስራቅ በኩል የበቀሉ የግንዱ ቅርንጫፎች ቆራርጣ ፀረ ድህነት ትግልዋን አጠናክራ  ቀጥላለች። ሻእብያ እንቅፋት ለመሆን በተጋደመበት እየበሰበሰ የኤርትራን ህዝብ "ስራ ስላጣ ወሬ ሲፈበርክ ነው የሚውለው" ሊጥ አስመስለው እህል የሚነግዱትን አለቃቸውም እያለ ከመንግሥትነት ወደ ተራ አለሌ ማፍያነት መቀየሩ ይፋ ሆኗል።